23 oktober 2017 00:33

# ኢትዮጵያ አደጋ ላይ ነው !!!

ኢትዮጵያ የግፉአን ምድር፤
የጥቃት ሰለባ የሆኑ ሰዎችና ግፉአን የሞሉበት አገር ኢትዮጵያ !። ትብብር፣ መረዳዳትና መተሳሰብ የኢትዮጵያዊ ነታችን መልካም ገጽታ መግለጫ ጠፍቶ በሃገራችን እየሆነያለው ነገር በጣም የሚያስፈ ራ ነው ሃገራችን እንደ ሃገር ህልውና እንዳይኖራት፤ ኢትዮጵያዊው ሕዝብ አብሮ መኖር እንዳይችል እገሌ ከዚህ ክልል እገሌ ከዚህ ክልል ውጣ እየተባለ በሰው ዘር ላይየሚፈጸም የሙብት ጥሰትና የፍ ትሕ መጓደል ሌላውን ሰው ሊያሳስብና እንቅልፍ ሊነሳው ይገባል። በውጥረትና በቀውስ የተሞላ የዘ ር ቅራኔዎችን እያየን ነው የሚታየውና የሚሰማው ውስጥን ያደማልከአገርነት ተርታ በሚያወጣ ቋፍ መገኘታችን ሕይወት ውሸት ሲሆን በጣም ያስፈራል፡
፡ የኢትዮጵያ መከራ የከፋ ሆኗል! የሚሰማ ቢገኝ የጣና ሐይቅ እየነገረን
ነው ! ዛሬ የኢትዮጵያ ጠላቶች ጠላቶቻችንድምበር ጥሰው፣ ወታደር አሰልፈው፣ ጦር ሰብቀው አገር መውረር አያስፈልጋቸውም። እግራቸው ካገራቸው ሳይወጣ በዕጅ አዙር በለየላቸው ጨካኝ የአገር ትርጉም በማይገባቸው ወያኔ አገዛዝ ከእኛሊወስዱ የሚፈልጉትን መውሰድ ይችላሉ ኢትዮጵያ ስሟ ን እየጠሩ መደበቂያ አድርገዋታል ። እራሳችንን እንጠይቅ!? ዛሬ አንዱ ግፉአ አንዱ ተመልካች አን ዱ ሯጭ የሚሆንበት የ ዝምታ ህመም ጊዜአይሆንም።
ይህ ደግሞ በትውልዱ በኢትዮጵያዊው በእኛ ትከሻ ላይ ያረፈ ችግር ነው ያገባናል! ላጥፊዎቹ አሳዳ ጆች መደበቂያ ጫካ ሆነን ኢትዮጵያዊያን እስከ መ ቸ መንገድ ላይ እንቅር? ብንጠላውምታስረን እ ስከኖረን ድረስ መጠቃታችን አይቀርም።
እስከመቼ ኢትዮጵያዉያን ተስፋ ቆርጠን?! ፎጣችንን መሬት ላይ ጥለን፣ አምባገነንነትን አሜን ብ ሎ የመቀበል አዝማሚያ አሳየን እስከመቼ !ኢትዮጵያዉያን መንቃት አለብን ትላንት ወድቀናል ብለ ን ዝም ብሎ መቀመጥ እስከመቼ የትናንቱ ጠባሳችንን እያየን ወደፊት ከመራመድ እንቆጠብ ! ከስህ ተቶቻችን ተምረን፣ በቁርጠኝነት መነሳት ግድነዉ። ቁልፉ በእጃችን ነዉ። በርግጥ ለዉጥ ማምጣት እንችላለን ኢትዮጵያዉያን !!!እስከ መቸ ታስረን እንኑር !!!? ጆሮ ያለው ይስማ ኢትዮጵያ አደጋ ላ ይ ወድቋል ልንታደገው ይገባል!!! የጣና ሐይቅእየነገረን ነው በፍፁም አናፈግፍግ፡፡
በፍፁም አንዘናጋ፡ በዝምታ ከሞት ማምለጥ አይቻልም፡
፡ ጆሮ ያለው ይስማ ኢትዮጵያ አደጋ ላይ ነው !!!
በቀደመው ታሪኩና በብሔራዊ ማንነቱ የሚኩራው የኢትዮጵያ ህዝብ ነው !!!

*ገብርኤል ብዙነህ*

*10/22/2017*